# በዓለም አቀፍ ደረጃ ክብርና ዝናን የተጎናፀፈው ሠራዊታችን

## (ክፍል አንድ)

**ሱራፌል ዓለሙ 12-25-14**

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በመደበኛነት ከተቋቋመበት ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ በህዝቡ በሚያገኘው ድጋፍ እየታገዘ የተሰጠውን ህገ-መንግስታዊ ተልዕኮ አንግቦ ሀገራችንን ከውስጥም ይሁን ከውጭ ፀረ-ሰላም ኃይሎችና አሸባሪዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ተከላክሏል፤በመከላከል ላይም ይገኛል። በዚህም በሀገራችን ውስጥ እየተካሄደ ላለውና ህዝቡን በየደጃው ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ለሚገኘው ፈጣንና ተከታታይ ልማታዊ ዕድገት የበኩሉን ሚና ተጫውቷል። እየተጫወተም ነው።

እርግጥ ሠራዊቱ ከሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት በሀገሪቱ ውስጥ እተመዘገበ ያለው የልማት ዕድገት ያለ አንዳች መስተጓጎል ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥልና ህዝባችንም በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን የማይተካ አስተዋፅኦ ማድረጉን ለውድ አንባቢዎቼ ማውሳት “ለቀባሪው የማርዳት” ያህል ይሆንብኛል። ምክንያቱም ታታሪውና ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላማችንን ለማደፍረስ የሚሯሯጡ የሻዕቢያ ቅጥረኞችንና የተዳከመች ኢትዮጵያን ለማየት የሚሹ ኃይሎችን በተለያዩ ወቅቶች አይቀጡ ቅጣትን በመቅጣት አንገታቸውን እንዳስደፋቸውና የተላኩትን መልዕክት ሳደርሱ መንገድ ላይ ደፍቆ እንዳስቀራቸው በሚገባ ስለሚያውቅ ነው። ለጠላቶቹ እሳት የሆነው ክንዱ የሚፋጅ፣ ነገር ግን ሁሌም ለህዝብ በመወገንና በተልዕኮዎቹ ሁሉ ህዝብን ማዕከል አድርጎ የሚንቀሳቀስ ህዝባዊ የሰላም ሰራዊት መሆኑም የአደባባይ ምስጢር መሆኑም እንዲሁ።

መከላከያ ሰራዊታችን “ከራስ በፊት ለህዝብና ለሀገር” የሚል እሴትን ተላብሶ የተገነባ እንደመሆኑ መጠን፣ በተሰማራባቸው ተልዕኮዎቹ ሁሉ ህዝብን ሳያቅፍና ከዕለት ጉርሱ ለህዝቡ ሳያከፍል፣ አቅመ-ደካማዎችንና ችግረኞችን ሳይረዳ፣ ትምህርት ቤቶችን ሳይሰራ፣ እንዲሁም አቅሙ በፈቀደ መጠን እንደ ማንኛውም ዜጋ ከሚያገኘው ደመወዝ ለልማት እጆቹን ሳይዘረጋ ግዳጁን የተወጣበት ወቅት አለ ለማለት አያስደፍርም። ከህዝብ አብራክ

የወጣ ሃይል ስለሆነም እያንዳንዷን ተልዕኮዎቹን ከህዝብ ጋር ተሳስሮ የሚፈፅም የህዝብ ልጅ ነው። ታዲያ ይህን ዕውነታ በሀገር ውስጥ ከሚያደርገው ወሳኝ ህዝባዊና ህገ-መንግስታዊ ተግባራቱ አኳያ ብቻ መመልከት አይቻልም–በውጭም ቢሆን በዓለም ላይ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሁለት ተፋላሚ ወገኖች ሳይቀር "እርሱ በመካከላችን ገብቶ ሰላማችንን ያረጋግጥልን" እስከ መባል የደረሰና ህዝባዊ አመኔታን ያተረፈ የህዝብ ወገን ነው። ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ ይህ ዝና ሃያ ዓመት ባልሞላ አጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘ መሆኑን ልብ ይሏል!

ይህ ህዝባዊ ወገንተኛ ኃይል በተሰማራባቸው ተልዕኮዎቹ ሁሉ የድሉ ምስጢር ህዝባዊነቱ፣ የዓላማ ፅናቱና ጀግንነቱ እንዲሁም ግዳጆቹን በሙሉ እንደ አንድ ቤተሰብ ተሳስሮ የሚፈፅም አሃዳዊ ጥንካሬ (Unit Strength) ያለው መሆኑን ከጎረቤቶቻችን ባሻገር ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም መስክሮለታል። አክብሮትና ዝናም ችሮታል። ለዚህም በእማኝነት በተለያዩ ጊዜያት በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች መመረጡና በተግባርም ያከናወናቸውን አብነታዊ ሃቆችን መጥቀስ የሚቻል ይመስለኛል። ይህም ሰራዊታችን ከህዝባዊ ባህሪያቱ በተጨማሪ፣ የሰላም ዘብ ሆኖ የተሰጠውን ግዳጅ በብቃት እየተወጣ ዛሬ ላይ የደረሰ ህዝባዊ ኃይል መሆኑን ያመላክታል። እናም "ነገርን ከመሰረቱ" እንዲሉ አበው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንቱታን ያተረፈውን ሰራዊት ዝናዎችን ከሰላም ጠባቂነቱ አኳያ መዳሰሱ ተገቢ ይመስለኛል።

## ቀደምት ፍፃሜዎች

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት በአዲስ መልክ በአዋጅ ከተቋቋመበት ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሰላም ጠባቂ ሆኖ ሲሰማራ ከህዝቡ ጋር በመሆን በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። በሀገር ውስጥ አስተማማኝ ሰላምን ከመፍጠር አኳያ የመጀመሪያው ሰላምን የማስጠበቅ ተልዕኮ የተወጣው አል-ኢትሃድ አል-ኢስላሚያ የተሰኘው የሽብር ቡድን የሰነዘረውን የትንኮሳ ሴራ ተከትሎ እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያስታውሰው ይህ አሸባሪ ቡድን በሀገራችን ላይ ጥቃት ለመሰንዘር በማሴር ራሱን ሲያደራጅና ሲያዘጋጅ ነበር፡፡ ቡድኑ በወቅቱ መንግስት አልባ ከነበረችው ሶማሊያ ወደ ሀገራችን በመስረግ የሽብር ጥቃት ይሰነዝር ነበር፡፡ ለዚህም

በዋነኛነት እንደ መተላለፊያ የተጠቀመበት የምስራቁ የሀገራችንን ክፍልን እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና የቡድኑ እኩይ ሴራ የአካባቢው ህዝብና መስተዳድር በህገ-መንግስቱ ያገኘውን ጥቅምና መብት የሚያሳጣውና ሰላሙንም የሚያናጋ መሆኑን በውል በመገንዘሙ ለሠራዊታችን መረጃ በመስጠት ከጐኑ ሊቆም ችሏል፡፡ መከላከያ ሰራዊታችንም ቀደም ባሉት ጊዜያት በአካባቢው ባከናወናቸው ህዝባዊ ተግባራቱ ሳቢያ የህዝብን ፍቅርና አመኔታ ያገኘ ስለነበር፤ የአካባቢው ህዝብም ከአብራኩ የወጣው ልጁ በተዋጽኦ የተካተተበትን ሠራዊት በፅናት ደግፎ ተንቀሳቅሷል፡፡ ህዝቡም ሠራዊታችንም ይህንን መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ በአጭር ጊዜ ዝግጅት አሸባሪው ቡድን ዝግጅት ያደርግባቸው ወደነበሩት ቢልሃዋና ሉቅ በሁለት አቅጣጫ በመወርወር የሽብር ቡድኖቹ ባልገመቱበትና ባላሰቡት ሰዓት ወደ ካምፓቸው ዘልቆ በመግባት በታትኗቸው የነበረውን የፀጥታ ስጋት ተወገደ፡፡

ሌላኛው ደግሞ የኤርትራ መንግሥት ድንገተኛና ያልታወጀ የእብሪት ወረራ ነው። የእብሪት ወረራው ልማታዊ መንግስታችንና ህዝባችን ያልጠበቁት ብቻ ሳይሆን፣ በዋና ጠላታችን ድህነት ላይ አትኩረው ይሰሩም ስለ ነበር እምብዛም ዝግጅት አልነበረም፡፡ ይህ ወረራ ሠራዊታችን ለጦርነት ባልተዘጋጀበት ሁኔታ ከመቃጣቱም በላይ፣ ሻዕቢያ ድምፁን አጥፍቶ በጣም የተዘጋጀበት ከመሆኑ አኳያ የሠራዊቱ የኃይል ሚዛን በቁጥርም በመሣሪያም የማይመጣጠን ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ህዝባዊ ባህሪይን የተላበሰውና በተጣሰው ድንበር አካባቢ የተሰለፈው ሰራዊታችን ከአቅሙ በላይ የሆነውን ወራሪ ኃይል መክቶ ባለበት እንዲገታ አስገድዶታል፡፡ ወራሪው ከተገታበት ሥፍራ ተጨማሪ ቦታዎች ለመያዝ የሞት የሽረት ጥረት ቢያደርግም፤ ቁርጠኛውና ዓላማ ፅኑው ሠራዊታችን ከአካባቢው ሕዝብ ጋር መተኪያ የማይገኝላት ሕይወቱን በመሰዋት በርካታ የሻዕቢያ ማጥቃቶችን ማክሸፍ ችሏል፡፡

ታዲያ ሠራዊታችን በእንዲህ ዓይነት ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈለ ባለበት ሁኔታ ነበር– መርሁ ሰላምና ሰላም ብቻ የሆነው መንግስታችን ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ ጥረት ሲያደርግ የነበረው። ዳሩ ግን ሻዕቢያ ፈቃደኛ ባለመሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወራሪውን ለመመከት ብሔራዊ ጥሪውን እንዲያስተላልፍ ተገድዷል፡፡ በጥሪው መሠረትም የመላው ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ወጣቶች የሀገራችንን ሉዓላዊነት በመስዋዕትነታቸው ለማስከበር ያላቸውን ቁርጠኝነት በመግለፅ አፋጣኝ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከባድ መስዋዕትነት በመክፈል ወራሪውን ገቶ የያዘውን የመከላከያ ሠራዊታችንን ክንድ ለማፈርጠምም ወደ ማሰልጠኛዎች ከተቱ፡፡ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በገንዘብና በቁሳቁስ ድጋፉን ለማድረግ በሁሉም ጫፎች ተነሳ፡፡ እናም በአጭር ጊዜ ውስጥ የሰራዊታችን አቅም በሰው ኃይል፣ በስንቅና በትጥቅ ተጠናክሮ ለወሳኙ ማጥቃት ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ ሀገራችንም ሳትወድ በግድ ወደ ጦርነት ለመግባት ተገድዳለች።

ጊዜው እየገፋ ሲሄድም የመከላከያ ሠራዊታችን ወራሪውን በመከላከል የውጊያ ስልት ካለበት እንዳይነቃነቅ ገትቶ ከመያዝ ጐን ለጐን፣ በወሳኝ ማጥቃት ጠላትን ደምስሶ ከግዛታችን ለማባረር የሚያስችለውን ፈታኝ ስልጠና ከምሽግ በስተጀርባ በማድረግ ተሰናዳ፡፡ ዝግጅቱም በደጀኑ ህዝብ ታግዞ ተጧጧፈ። እናም ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን በ1992 ዓ.ም በሁሉም ግንባሮች ማጥቃት በመሰንዘር የማይደፈሩ የሚመስሉትን የሻዕቢያን ምሽጐች እንደ ሰማያዊ መቅሰፍት ባልታሰቡ አቅጣጫዎች ወረደባቸው፡፡ አዎ! ወራሪው ሃይል የሠራዊታችንን ጥቃት መመከት ተስኖት በአገኘው ክፍተት ሁሉ እግሬ አውጪኝ ከማለት ያለፈ ምርጫ አልነበረውም፡፡

ሠራዊታችን በእንዲህ ዓይነት ተዓምራዊ ማጥቃት ባድመን ጨምሮ በወራሪው የተያዙ በርካታ ግዛቶቻችንን አስለቀቀ። ከዚህም አልፎ በርካታ የኤርትራ አካባቢዎችን ተቆጣጥሮ ወረራውን በወሳኝ መልኩ መቀልበሱን የሰላሙ ባለቤት ለሆነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበሰረ፡፡ ምንም እንኳን ሠራዊታችን በርካታ የኤርትራ ግዛቶችን የተቆጣጠረ ቢሆንም፤ በመንግሥታችን ፖለቲካዊ ውሳኔ መሠረት ከኤርትራ ግዛቶች ለቆ በመውጣት ወደ ሀገሩ ተመልሶ ለጀመርነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለፀረ-ድህነት ትግላችን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ስራውን ለመጀመር ችሏል፡፡ ታዲያ ወራሪው ሻዕቢያ በጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን በኃይል ተደምስሶ ከወጣ በኋላ የዘመቻው አቅጣጫ በድህነት ላይ ማነጣጠር ነበረበት፡፡ እናም ድሮም ቢሆን ተገዶ እንጂ ፈልጐ ወደ ጦርነት ያልገባው መንግሥታችንና ሰላም ወዳዱ የሀገራችን ህዝብ ወደ ልማት አጀንዳቸው ተመልሰዋል፡፡

ይሁንና "በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል" እንደሚባለው፣ አሁንም በያኔዋ መንግስት አልባዋ ሶማሊያ ውስጥ የተሸሸጉና ራሳቸውን "እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት" እያሉ የሚጠሩ አክራሪዎች በሀገራችን ላይ የጀሃድ ጦርነት አውጀዋል። በወቅቱ በሼህ ዳሂር ሃዌይስ ይመራ የነበረውን ይህ ፅንፈኛ ቡድን ተጨባጭና ድርስ አደጋ ለመበታተን

እንዲሁም አልሸባብን በማዳከም ያከናወነው ሰራዊታችን ጀግንነታዊ ተግባር ፈፅሟል፡፡ እንደሚታወቀው የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት በማለት ራሱን የሚጠራው የእስልምና አክራሪዎች ቡድን፤ በኤርትራ መንግስት አይዞህ ባይነት በሀገራችን ላይ ግልፅ የሆነ ጦርነት አውጇል፡፡ ይሁንና መንግስታችን ሁኔታውን በከፍተኛ ተዕግስት ከማለፍ ባሻገር "ህብረቱ" ትክክለኛ አቋም እንዳልያዘ ለማስረዳት ብዙ ጥረት አደረገ። ሆኖም ተቀባይነትን ሊያገኝ አልቻለም፡፡

ታዲያ ይህን የተደቀነብንን ቀጥተኛ አደጋ ለማስወገድ ሠራዊታችን አክራሪ ሃይሉን ለመፋለምና ከምንጩ ለማድረቅ ወደ መንግስት አልባዋ ሶማሊያ ግዛት ማቅናት ግድ ሆኖበታል፡፡ በዚህም ከዳሂር ሃዌይስ ቡድን ጋር የኤርትራ መንግስት ወታደሮች፣ በአሳፋሪ ሁኔታ ሀገሩን ከድቶ ከጠላት ጋር ያበረው "ኦነግ" ፣ራሱን "ኦብነግ" እያለ የሚጠራው የሽብርተኞች ስብስብ እና ሌሎች ዓለም አቀፍ አሸባሪዎች አብረውት ቢሰለፉም፤ መከላከያ ሠራዊታችን በሶማሊያ ህዝብ ድጋፍ እየታገዘ "እስላማዊ ፍርድ ቤቶችን ህብረት" ከእነ ጀሌዎቹ ሊበታትነው ችሏል፡፡ ይህም በቅድሚያ በሀገራችን ላይ ተፈጥሮ የነበረውን የስጋት ደመና መግፈፍ ከመቻሉም በላይ፤ በአክራሪዎቹ ቁም ስቅሉን ሲያይ ለነበረው ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብም አንፃራዊ ሰላምን እንዲያገኝ አድርጓል፡፡

ዳሩ ግን ከ"እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት" መበታተን በኋላ በአምሳያው የተቀረፀው "አል-ሸባብ" የተሰኘው የአል-ቃይዳ የምስራቅ አፍሪካ የሽብር ክንፍም በሀገራችን ላይ ተመሳሳይ አደጋ መደቀኑ አልቀረም፡፡ ያልተጠናከረ የሽግግር መንግስት ባለባት በያኔዋ ሶማሊያ ውስጥ የመሸገው ይህ የሽብር ቡድን፤ እንደ "እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት" ሁሉ በኤርትራ መንግስት ሙሉ ድጋፍ በሀገራችን ላይ ጅሃድ አወጀ፡፡ ቡድኑ የአካባቢያችንና የሀገራችን ብሔራዊ ደህንነት ስጋት መሆኑን የተገነዘቡት የኢፌዴሪ መንግስትና ህዝባችን የሽብር ቡድኑን የጥፋት መንገድ በማያሻማ ሁኔታ በማወቃቸው እንዲሁም ተጨባጭና የቅርብ አደጋውን በመመልከታቸው፤ ሠራዊታችን አል-ሸባብን በማዳከም ስራ ላይ ወንድም ከሆነው የሶማሊያ ህዝብና ከሽግግር መንግስቱ ጋር አብሮ እንዲሰራ ወስነዋል፡፡

ሠራዊታችንም ብቃት ባላቸው ስትራቴጂዎችና ታክቲኮች እየተመራ በሶማሊያ ቆይታው ህዝባዊ የሰላም ዘብና የድል ሃይል መሆኑን በተግባር አረጋግጧል፡፡ ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብ አንፃራዊ ሰላምና ነፃነት እንዲያገኝም አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን አል-ሸባብ እና የራሳቸው ፍላጐት ያላቸው አንዳንድ ሃይሎች የፈጠራ ወሬን በመንዛት

ሠራዊታችን ከሶማሊያ ህዝብ ጋር ለማጋጨት ቢሞክሩም፣ የሠራዊታችንን የሰላም ሃይልነትና ህዝባዊነትን የተረደውን የዚያች ሀገር ህዝብ ቀልብ ሊስቡ ግን አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ሠራዊታችን በተግባር ተፈትኖ የሰላም ሃይልነቱን፣ የድል ሰራዊትነቱንና ህዝባዊ ወገንተኝነቱን በሶማሊያ ልሣነ-ምድር በማረጋገጡ አክራሪና አሸባሪ ሃይሎች ይበልጥ ከህዝብ እንዲነጠሉ አድርጓል፡፡ በዚህም የህዝቦች የሰላም ፍላጐት እንዲጠናከር ማድረግ ችሏል፡፡ ሠራዊታችን በእነዚህ ተግባራቶቹ የ"አል-ሸባብ"ን የጀርባ አጥንት በመስበር እና በማዳከም የተደቀነብንን ቀጥተኛ አደጋ ከማስቀረት ባለፈ፣ የሶማሊያ ህዝብም ከአክራሪዎች የፀዳ የራሱን ፌዴራላዊ መንግስት እንዲመሰረት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ የሰራዊታችን ሰላም ጠባቂነት በሀገር ውስጥ ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን ውድ አንባቢዎቹ ልብ ይሏል። እንደሚታወቀው የኢፌዴሪ ህገ - መንግስት አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ፣ "በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ" የሚል ድንጋጌን አስፍሯል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥረቶች ደግሞ በጠረጴዛ ዙሪያ ከሚደረጉ ድርድሮች እስከ የዓለም አቀፍ ህግን መሰረት በማድረግ የሚካሄዱ ወታደራዊ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ድረስ የሚዘልቁ ናቸው፡፡

የሰላም ማስከበር ተሳትፏችን በከፍተኛ ደረጃ ለዕድገቱ መሠረት የሆነው ግን ከደርግ ውደቀት በኋላ በሩዋንዳ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለማስቆም ሠራዊታችን ዘምቶ ሕዝባዊ ባህርይ በተላበሰ መንገድ የመጀመሪያውን ዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ በመወጣቱ ነው፡፡ ይህ ተልዕኮ ለመከላከያ ሠራዊታችን የመጀመሪያ ልምድ ቢሆንም ከተሃድሶው በኋላ በተጠየቀበት የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ጠንክሮ በመስራቱና ተወዳዳሪ ለመሆን ባሳያቸው ጥረቶች ተሳትፎው እየሰፋና ብስለት እያገኘ መጥቶ ዛሬ ለደረሰበት የዝና ደረጃ ለመድረስ በቅቷል፡፡

የሩዋንዳ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ህገ-መንግስቱ ከመጽደቁ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በሠራዊታችን የተከናወነው ነው፡፡ ይህ ግዳጅ፣ ህገ-መንግስቱ እየተረቀቀ በነበረበት ዓመት ውስጥም በመሆኑ የሠራዊቱን ህዝባዊ ባህሪይ የሚያመላክት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደሚታወቀው በወቅቱ በሩዋንዳ ውስጥ በሁቱና ቱትሲ መካከል በተነሳው የጎሳ ግጭት የዘር ማጥፋት ተግባር የተቀጣጠለበት ነበር፡፡ ይህን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለማስቆም የሚችል ኃይል አልነበረም፡፡ እናም የመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ መክሮ በ"UNAMIR" (የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተልዕኮ በሩዋንዳ) ጥላ ስር

ተሰማርቶ ተልዕኮውን ሊወጣ የሚችለው የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደሆነ በማመን ጥያቄውን ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት አቅርቧል፡፡

መንግስትም ሠላም ወዳድ በመሆኑና በሠራዊቱም ህዝባዊ አመለካከት ላይ ከፍተኛ እምነት ስለነበረው፣ አስቸጋሪውን ተልዕኮ ለመወጣት ቃል ገባ፡፡ "ጉና ሻለቃ" የተሰኘው የሠራዊታችን አካል ተዘጋጀች፡፡ አንዳንድ ተንታኞች "ሠላም ማስከበር በማይቻልበት ሁኔታ የመንግስታቱን ሠራዊት ለሰላም ጥበቃ መላክ መሰረታዊ ስህተት ነው" ወደ ተባለባት ሩዋንዳ ዘመቶ በአምባገነኑ የደርግ ሥርዓት ወቅት ተቋርጦ የቆየውን የሀገራችንን የሠላም ማስከበር ተሳትፎ በአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፈተው፡፡

ታዲያ በሩዋንዳው ተልዕኮ በሁለቱም ዙሮች የሠራዊታችን አባላት ግዳጃቸውን በብቃት በመወጣታቸው ተመድም ለፈፀሙት ክቡር ተግባር በወረታው ሜዳሊያ ሸልሟቸዋል፡፡ "ለህዝብ የወገነ ሠራዊት ለድል ይበቃል" ይሏል ይኼ ነው፡፡ ሩዋንዳ ከተረጋጋች በኋላም ቢሆን በሀገሪቱ 15ኛ የድል በዓል ላይ ለቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ለአቶ መለስ ዜናዊ መንግስታቸውና ሰራዊታቸው ለሠላም ባሳዩት ቁርጠኝነት የሀገሪቱን ታላቅ የኒሻን ሽልማት መስጠቷን እናስታውሳለን፡፡

ሠራዊታችን በብሩንዲ የተሰማራው በአፍሪካ ህብረት የሠላም ማስከበር ተልዕኮ (AMIB) ሌላኛው ተጠቃሽ ግዳጅ ነው፡፡ የአፍሪካ ህብረት በወቅቱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ለሠላም ማስከበር ተልዕኮ እንዲሰማራ ሲወሰን ሀገራችን ከምትከተለው የሠላም ፖሊሲ አኳያ አንድ ሻለቃን ወደ ብሩንዲ በመላክ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥታለች፡፡ በዚህም በብሩንዲ ያለውን የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮ በምክትል አዛዥነት መርታለች፡፡ ሠራዊታችን በብሩንዲው ተልዕኮን የተሰጠው ግዳጅ በተቃዋሚዎች መካከል የተደረሰውን የተኩስ አቁም ስምምነትን ተግባራዊነት መቆጣጠር፣ ትጥቅ ማስፈታት፣ ለመልሶ ግንባታ ፕሮግራም ምቹ ሁኔታን መፍጠር እና የሀገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ ነበር፡፡

ሠራዊታችንም በብሩንዲ ቆይታው እነዚህን ተልዕኮዎችንና የሚሰጡትን ማናቸውንም ግዳጆች በብቃት ከመፈጸም ባሻገር፣ ከባህሪው በመነጨ ሰፊ ህዝባዊና ሰብዓዊነቱ የሚያስገድዱትን በጎ ተግባሮች በመከወን ከህዝቡና ከብሩንዲ መንግስት አካላት ፍቅርና አክብሮትን አግኝቷል፡፡ በአፍሪካዊ ወንድማዊ መንፈስ የህዝቡን ችግር በመጋራት

በዚያች ሀገር ዜጎች ውስጥ ትልቅ ትዝታን ጥሎ አልፏል፡፡ ሠራዊታችን በዚያች ሀገር ውስጥ ካከናወናቸው በርካታ የህዝባዊ ወገንተኝነት ተግባራት ውስጥ ሁለቱን በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወላጆቻቸውን ላጡ ህጻናት ያደረገው ድጋፍ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በጦርነት ለተፈናቀሉ የሀገሪቱ ዜጎች ያደረገው እገዛ ተጠቃሽ ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በላይቤሪያ መንግስትና በተቀናቃኝ ኃይሎች መካከል በተፈጠረው ግጭት ሳቢያም ሰራዊታችን በሰላም ማስከበር ተልዕኮ እንዲሳተፍ ተጠይቋል። የመንግስታቱ ድርጅት አባል ሀገራቱ በመንግስታቱ ድርጅት የሠላም ማስከበር ተልዕኮ በላይቤሪያ (UNMIL) በአፋጣኝ ኃይል እንዲያሰማሩ ጥሪ ሲያቀርብ፤ የአፍሪካዊያንን ችግር እንደ ራሱ ችግር የሚመለከተው መንግስታችን ጥሪውን ለመቀበል አላቅማማም፡፡ እናም ሀገራችን በ1996 ዓ.ም በመጀመሪያውን ዙር 1784 የሰላም አስከባሪ ኃይል ወደ ላይቤሪያ አሰማርታለች፡፡

እናም ሠራዊታችን ቀጣና አራትን እየተባለ የሚጠራውንና ከስድስት ክፍላተ ሀገር በላይ የሚሸፍነውን ሰፊ ቦታ ፀጥታ እንዲያስከብር ሰጥቶታል፡፡ የመንግስታቱ ድርጅት የሠራዊታችንን ተልዕኮ አፈጻጸም ጥራትና ጥንካሬ እንዲሁም ለህዝብ ወገኖ እንደሚሰራ በመተማመን ይህ ክልል በሌሎች ሠላም አስከባሪ ኃይሎች እጅግ የሚፈራና በርካታ አማፂያን በመሸሸጊያነት የሚጠቀሙበት ነበር፡፡ ዳሩ ግን ሠራዊታችን የቦታው ውስብስብነት ሳይበግረው፤ በሠላም ማስከበር ያካበተውን ልምድ ተጠቅሞ እንዲሁም ህዝባዊ ባህሪውን ሰንቆ በላይቤሪያ ሠላምና መረጋጋትን በማስፈን፣ የተቃዋሚዎችን ትጥቅ በማስፈታት፣ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና በመልሶ ግንባታ እንቅስቃሴ ላይ ቀጥተኛ የልማት ተሳትፎ በማድረግ ግዳጁን ከህዝቡ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በአኩሪ ሁኔታ ሊፈጽም ችሏል፡፡

ቀደም ሲል ጫካውንና ደኑን በመመከት “ማንም እዚህ መጥቶ ሊያነቃንቀን አይችልም” ሲሉ የነበሩትና ህዝቡን ሲያሰቃዩና ሲያውኩት የከረሙት አማፂያን ሳይቀሩ የሠራዊታችንን ህዝባዊ ዓላማና ፍቅር ተገንዝበው ወደ ህብረተሰቡ ሊቀላቀሉ ችለዋል፡፡ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሠራዊታችን ካለው ቀለብ በመቀነስ ለተቸገሩ ላይቤሪያዊያን በመስጠት እንዲሁም በመንገድ ግንባታ፣ በድልድይ ስራ ወዘተ. በመሳሰሉ ልማታዊ ተግባሮች በመሳተፍ ከራሱ በፊት ለህዝብ የቆመ ኃይል መሆኑን አስመስክሯል፡፡ ከዴሞክራሲያዊ

አስተሳሰቡ በመነጨም በዚያች ሀገር ምርጫ እንዲካሄድ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡ መከላከያ ሰራዊታችን የተጎናፀፈው ዓለም አቀፋዊ ክብርና ዝና ካለው ህዝባዊ ባህሪይ፣ ጀግንነትና ግዳጅን እንደ አንድ ቤተሰብ የመፈፀም ባህሉ በተጨማሪ በውስጡ ያለው ጠንካራ ዲሲፕሊንም የድሉ ምስጢሮች ናቸው ማለት ይቻላል። እነዚህ ምስጢራቱም ዛሬ ላይ ለደረሰበት "አንቱታ" እና የገዘፈ ስብዕና የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል ማለት ይቻላል። እርግጥ ሰራዊቱ በተሰማራባቸው ማናቸውም ግዳጆች ህዝብን ከጎኑ ማሰለፉና የተሰጠውን ተልዕኮ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ኪሳራ በላቀ ውጤት የሚፈፅም መሆኑ የተፈላጊነቱ ሌላኛው ምስጢር ነው ሊባል ይችላል።

**ይቀጥላል…**